**የASPIRE ፖሊሲን እና ቴክኒካዊ መመሪያን**
ለማካተት የቀረበ አቤቱታ
ለህዝብ አስተያየት ክፍት የነ
የህዝብ አስተያየት እስከ ኤፕሪል 8፣ 2024 ድረስ እንቀበላለን

---

**ማጠቃለያ፥** የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ (DC PCSB) ህዝቡ በአሁኑ ጊዜ የአፈጻጸም አስተዳደር ማዕቀፍ (PMF) ተብሎ በሚጠራው የተጠያቂነት ስርአቱ ላይ አስተያየቶችን የሚሰጥበት ዕድል ማዘጋጀቱን ያሳውቃል። የዲሲ PCSB ሰራተኞች PMF አመታዊ የት/ቤት አፈፃፀም መረጃ ጠቋሚ ሪፖርት እና ግምገማ (ASPIRE) ስርዓት ተብሎ እንዲጠራ እንዲሁም የተስተካከሉ አካዴሚያዊ ተጠያቂነት ክፍሎችን እና የሥራ ደንቦች እንዲቋቋሙ የሚጠይቅ ሀሳብ አቅርበዋል። የቀረበው የASPIRE ፖሊሲ እና ቴክኒካዊ መመሪያ የስርዓቱን የተጠያቂነት ክፍሎች እና የሥራ ደንቦችን ይገልጻል።

የዲሲ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ እንደሚያገለግሉ ለመለካት የዲሲ PCSB ሰራተኞች የASPIRE ስርዓትን ነድፈዋል። ASPIRE አምስት ማዕቀፎች አሉት፥ ቅድመ መዋለ ህፃናት (PK) -ብቻ፣ PK-8፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የአዋቂዎች ትምህርት፣ እና አማራጭ ተጠያቂነት። እያንዳንዱ ማዕቀፍ ከሶስት እስከ አራት ምድቦች ያለውን አፈጻጸም ይገመግማል—የትምህርት እድገት፣ የትምህርት ቤት ስኬት፣ የትምህርት ቤት አካባቢ እና ትምህርት ቤት-ተኮር አፈጻጸም። በአጠቃላይ፣ እያንዳንዱ ምድብ በሚሰጣቸው ነጥብ የሚገለጹ የመመዘኛ ደረጃዎች ወይም ከፕሮግራሙ ጋር የሚቀራኙ መለኪያዎች አሉት። የህዝብ ቻርተር ካምፓሶች የመለኪያ ነጥቦችን ይሰበስባሉ እንዲሁም የASPIRE ነጥብ ያገኛሉ።[1] እነዚህ ውጤቶች የት/ቤት አፈጻጸምን ከሚገልጹ የASPIRE ደረጃዎች ጋር ይዛመዳሉ፥ አርአያነት ያለው፣ ጠንካራ፣ አጥጋቢ፣ ደካማ ወይም አጥጋቢ ያልነ።

የASPIRE ስርአትን ለማጠናከር፣ **"አዲስ መንገድ ለቻርተር ትምህርት ቤት አካዳሚክ ተጠያቂነት"** የሚል ነጭ ወረቀት አውጥተናል። ይህ ወረቀት የዲሲ PCSBን የአካዳሚክ ተጠያቂነት ታሪክ፣ የተጠያቂነት ማዕቀፎቻችንን የምንከልስበት ምክንያት፣ እና እንዲሁም ዋናዋናዎቹን የ ASPIREክፍሎች እና ከሱ ጀርባ ያለው የምርምር መሰረት ለማጋራት ያለመ ነው። ወረቀቱን [እዚህ](#) ያንብቡ።

**ህዝባዊ ስብሰባዎች፥** ሕብረተሰብ የሚሳተፍባቸው ስብሰባዎች ይኖራሉ፥ ማርች 10፣ 2024 ከቀኑ 6:00 እና ኤፕሪል 8፣ 2024 ከቀኑ 6:00 ሰዓት ድምጽ የሚሰጥበት ጊዜ ጁን 10፣ 2024 ከቀኑ 6:00 ሰዓት ይናል። እባክዎ ለመመዝገብ www.dcpcsb.org/events ይጎብኙ።

**የህዝብ አስተያየት መመሪያዎች፥** አስተያየቶች ከኤፕሪል 8 ቀን 2024 በፊት ወይም በዚሁ ቀን መቅረብ አለባቸው።[2] ከሚከተሉት ዘዴዎች አንዱን በመጠቀም በ"ASPIRE ፖሊሲ እና ቴክኒካል መመሪያ - የህሳቤ ይካተትልኝ አቤቱታ ሰነድ" የተለዩ አስተያየቶችን ማስገባት ይችላሉ።

1. ወደ https://dcpcsb.org/public-comment በመሄድ በሕዝብ ተሳትፎ ስብሰባው ላይ ማስረጃዎትን ለማቅረብ ይመዝገቡ። ቅጹን ለመሙላት "በስብሰባ ላይ ለመመስከር ይመዝገቡ" የሚለውን ትር ጠቅ ያድርጉ። ለመመስከር የመመዝገቢያ ቀነ-ገደብ ማርች 10፣ 2024 እኩለ ቀን ወይም ኤፕሪል 8፣ 2024 እኩለ ቀን ነው።
2. የጽሁፍ አስተያየት በሚከተለው አማካኝነት ያስረክቡ፥
    a. የኦንላይ ቅጽ በ https://dcpcsb.org/public-comment

---

1 በአማራጭ ተጠያቂነት ማዕቀፍ የተገመገሙ ትምህርት ቤቶች የASPIRE ነጥብ አያገኙም።
2 ዲሲ PCSB መብቱ የተጠበቀ ነው፣ ነገር ግን የተላከለት ይዘት በከፊል ወይም በሙሉ ብልግናዊ አገላለጾችን ያካተተ በመኑ ለህትመት አይበቃም ብሎ ባመነ ጊዜ ይዘቱን የመገምገም፣ አስቀድሞ የማየት፣ የማጣራት፣ የማረም፣ ውድቅ የማድረግ፣ ወይም የማስወገድ ግዴታ ግን የለበትም።

b. በፖስታ መልእክት፣ በአካል ይዞ መምጣት ወይም በመልእክተኛ፥ ትኩረት፥ የሕዝብ አስተያየት፣ የዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ፣ 3333 14th Street NW፣ Suite 210፣ ዋሽንግተን ዲሲ 20010።

እባክዎን ዲሲ PCSB የጽሑፍ አስተያየቶችን የሚቀበለው ከህዝባዊ ስብሰባው አንድ ቀን በፊት ከቀኑ 11:59 በፊት ወይም በዚሁ ሰአት እንደነ ልብ ይበሉ።

3. የድምጽ ምስክርነት በስልክ ያቅርቡ፥ በ (202) 328-2660 ይደውሉ እና አማራጭ 2ን ይምረጡ። (ምስክርነትዎን ለመቅረጽ እስከ አምስት ደቂቃ ድረስ ይኖሮታል። እባክዎ ሁሉም አስተያየቶች ወደ ጽሑፍ እንደሚቀየሩ እና ለህዝብ እንደሚደርሱ ልብ ይበሉ።

**ለተጨማሪ መረጃ፣** የት/ቤት አፈጻጸም ዲፓርትመንት ዳይሬክተር የኑትን Kirsten James ን በ kjames@dcpcsb.org ወይም በ (202) 328-2207 ያግኙ።